**እንኳን ደህና መጡ**

**Amharic/አማርኛ**

***ወደ ምእራብ አውስትራሊያ እንኳን ደህና መጡ***

ምእራብ አውስትራሊይ ከሌሎቹ ክፍለ ሃገሮች ይልቅ በርካታ የባህል ስብጥር ያለባት ክፍለ ሃገር ናት። ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚደርሱት ኗሪዎቿ ወይም አንድ አራተኛው (27%) የምእራብ አውስትራሊያ ሕዝብ የተወለደው ከባህር ማዶ ነው። በምእራብ አውስትራሊያ ከ200 ሃገራት በላይ የመጡ ሕዝቦች ይኖሩባታል፤ የሠሩባታል እንዲሁም ይማሩባታል። እስከ ሁለት መቶ የሚደርሱ ቋንቋዎች ሲነገሩባት ከመቶ በላይ ሃይማኖቶችና እምነቶችም ይታመናሉ።

ይህ ድህረገጽ መጠነ ሰፊ የሆነ በሁሉም መንገድ ማለትም፤ በዚች ታላቅ ክፍለ ሃገራችን፤ በማህበራዊ፤ በኢኮኖሚና በባህላዊ ሕይወት ለመሳተፍ የሚያስችልዎና የሚረዳዎ ሰፋ ያለ የመረጃ ምንጭ ይሆንልዎታል።

## የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ (Office of Multicultural Interests (OMI))

የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ የአካባቢ መንግሥት መምሪያ አንድ ክፍል ነው። የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ የክፈለ ሃገሩን መንግሥት የእድገት መመሪያ ይደግፋል። በተጨማሪም የመድብለባህላዊነትን መርሃግብር እና የተለያየ የባህል፤ የቋንቋና የሃይማኖት ልምድ ላላቸው ምእራብ አውስትራሊያውያን መድብለባህላዊነትንና የተሻለ አገልግሎት የሚያገኙበትን ዘዴ ያራምዳል። የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ በሕዝብ መሥሪያ ቤቶች፤ በምእራብ አውስትራሊያ ህብረተሰብና በንግድ ድርጅቶች፤ መተሳሰርንና ሁሉንም የሚያካትት ብሎም አምራች የሆነ ህብረተሰብ ለማፍራት መድብለባህላዊንትን በተመለከተ በመሪነት ይሰለፋል።

የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ 'የ2009-2013 የአላማ ግብ እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፤

- **ተሳትፎ -** በባህልና በቋንቋ የተለያየ (CaLD) ተብሎ የሚጠራው የህብረተሰብ ክፍል በማህበረሰብ፤ በኢኮኖሚና በባህላዊ ህይወት ሙሉ ተሳፎ እንዲያደርግ፤
- **እኩልነት -** በባህልና በቋንቋ የተለያየው ማህበረሰብ በእኩልነት ለመሳተፍ የማያስችሉትን ልምዶች መቅረፍ፤
- **ማዛመት -** የምእራብ አውስትራሊያን የባህልና የቋንቋ መሰባጠር ጠቃሚነት ማዛመት።

የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ ለዜግነት፤ ለቪዛ ወይንም የስደትን ጉዳይ በተመለከተ ሃላፊ አይደለም። ስደትን እና የአውስትራሊያ ዜጋ መሆንን በተመለከተ፤ እባክዎን የስደትና የዜግነት መምሪያን በስልክ ቁጥር 13 1881 ደውልው ያንጋግሩ፤ ውይንም ድህረገጻቸውን www.diac.gov.au ይመልከቱ።

## መመሪያዎችና መርሃግብሮች

### የቋንቋ አገልግሎት

የ2008 የቋንቋ አገልግሎት መመሪያ፤ የመላው ምእራብ አውስትራሊያ መንግሥት መመሪያ ነው። አላማውም አገልግሎት ለሚፈልጉ ግለሰቦች ሁሉ፤ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የችግር መንስኤ መሆን እንደማይኖርበት ያረጋግጣል። ከምእራብ አውስትራሊያኖች መካከል በተገቢው መንገድ ግንኙነት ለማድረግ እርዳታ የሚፈልጉ፤ የሃገሩ ተወላጆች (አቦሪጅናሎች)፤ ስደተኞችና ደንቆሮዎች ወይንም መስማት የተሳናቸው ናቸው።

ወደ መንግሥት ቢሮዎች በሚሄዱበት ጊዜ በእንግሊዝኛ ግንኙነት ለማድረግ እርዳታ ካስፈለገዎ ትርጁማን መጠየቅ ይችላሉ፤ ትርጁማንም በነፃ ይሰጥዎታል። ለዚህ እንዲረዳዎት፤ የምእራብ አውስትራሊያን የትርጁማን ካርድ መጠየቅ ይችላሉ።.

የትርጁማን ካርድ ለማግኘት፤ እባክዎን በቅርብዎ የሚገኘውንና *‘በምእራብ አውስትራሊያ አዲስ መጦች መመሪያ’* በሚለው ዝርዝር ስር፤ የሰፈራ አገልግሎት ሰጪውን ድርጅት፤ ህትመት በሚለው የድህረገጽ ክፍል ፈልገው ይገናኙ።T

የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ (OMI) ትርጁማንን በተመለከተ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላል። እባክዎን ለተጨማሪ መረጃ በዚህ ድህረገጽ ላይ የቋንቋ አገልግሎት የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

### የማህበረሰብ የገንዘብ ስጦታ መርሃግብር

የመድብለ ባህል ፍላጎት ቢሮ፤ የማህበረሰብ የገንዘብ ስጦታን (CGP) የሚለውን መርሃግብር ያስተዳድራል። የመርሃግብሩ አላማ፤ የመድብለ ባህል ፍላጎት ቢሮን አላማ፤ ተሳትፎን፤ እኩልነትንና ሁሉንም ማለትም አጥሮችን በማስወገድ የባህል ተሳትፎ እንዲኖር የምእራብ አውስትራሊያውያንን ተግባሮችና ድርጊቶች ያዛምታል። T

መሰረታቸውን በምእራብ አውስትራሊያ ያደረጉና በትርፍ ላይ ሳይመሰረቱ ህጋዊነት ያገኙ የህብረተሰብ ድርጅቶችና ቡድኖች፤ ለገንዘብ ስጦታ ማመልከት ይችላሉ። የስጦታው አይነት በሁለት የከፈላል - ህብረተሰቦችን የሚያጎለብት ፕሮጄክት (እስከ $15 000 ዶላር ድረስ አለ) እና ባህላዊ ልውውጥን አስመልክቶ ለሚደረጉ ዝግጅቶችና አከባበሮች (እስከ $5 000 ዶላር አለ) ይሰጣል።

የመድብለ ባህል ፍላጎት ቢሮ (OMI) ማመልከቻችሁን ለመቀበልና የምእራብ አውስትራሊያን ማህበረሰብ ለመጥቀም ከእናንተ ጋር ሆኖ ለመሥራት እየተጠባበቀ ነው። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትም ሆነ ከዚህ በፊት የገንዘብ ስጦታውን ስላገኙ ደርጅቶች ለማወቅ ወይንም ድርጅትዎ ማመልከት ይችል እንደሆን ለማረጋገጥ ወይንም ከማመልከትዎ በፊት ስለአሰቡት ፕሮጀክት ሊያወያዩን ከፈለጉ፤ እባክዎን የገንዘብ ስጦታውን ተጠሪ ያነጋግሩ።.

የመመሪያውን ግልባጭም ሆነ የማመልከቻ ቅጽ ከፈለጉ፤ ለተጨማሪ ዝርዝር መረጃ፤ በዚህ ድህረገጽ ላይ፤ የማህበረሰብ የገንዘብ ስጦታ በሚለው ስር ይመልከቱ።

### መግለጫዎችና ህትመቶች

የተለያዩና ሰፋ ያሉ መግለጫዎችና ህትመቶች፤ እስታትስቲክስን ጨምሮ፤ በምእራብ አውስትራሊያ የባህል ስብጥር፤ አገልግሎት ሰጪዎችን በተመለከተ የባህልና የአካባቢ መመሪያዎችና ለትምህርት ቤት የትምህርት መረጃዎችን ጨምሮ በድህረገጹ ላይ ያገኛሉ። ወደምእራብ አውስትራሊያ አዲስ መጤ ከሆኑ፤ የአዲስ መጤዎች የመመሪያ አገልግሎት የሚለው በተለይ ሊጠቅምዎት ይችላል።

**ለምእራብ አውስትራሊያ አዲስ መጤዎች የመመሪያ ዝርዝር**
በምእራብ አውስትራሊያ፤ አካባቢዎን ለመልመድና ያሉትን የመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የንግድ ቡድኖችን ለማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

በ2010 የወጣው፤ *‘ለምእራብ አውስትራሊያ አዲስ መጤዎች የመመሪያ ዝርዝር’*፤ የ2005ቱና ተሻሽሎ የወጣና በጣም ተውዳጅ የነበረው መመሪያ ሲሆን፤ በተቀላጠፈ መንገድ ከአንድ ቦታ ወደሌላው መሄድ እንዲችሉና ከአንድ ምንጭ ብቻ ማግኘት የሚችሉት የመንገዶች ካርታም አለው።

መመሪያው መኖሪያ ቤትን፤ ሥራን፤ ትምህርትን፤ ጤናን፤ መጓጓዣን፤ የልጆች እንክብካቤን እና የህግ አገልግሎትን እንዲሁም ኮመንዌልዝን፤ ክፍለ ሃገርን እና የአካባቢ መንግሥታትን በተመለከተ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችና የግንኙነት ዝርዝሮችን ይሰጣል።

እባክዎን በዚህ ድህረገጽ ላይ ህትመት በሚለው ስር፤ *‘ለምእራብ አውስትራሊያ አዲስ መጤዎች የመመሪያ ዝርዝር’* የሚለውን ይመልከቱ።

**ዘረኝነትና ዘርን አስማልክቶ ጥቃት ድርሶብዎታል?**
ዘርን እና ሃይማኖትን አስመልክቶ አድልዎ ማድረግ ወይንም ግለሰብን በተገቢው መንገድ አለማስተናገድ ሕገ ወጥ ነው።

ዘርን አስመልክቶ ደርሶብኛል የሚሉት በደል ካለ፤ ሁኔታውን ለምእራብ አውስትራሊያ ፖሊስ እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ። የምእራብ አውስትራሊያ ፖሊስ የእርዳታ ማእከልን በስልክ ቁጥር 131444 ማግኘት ይችላሉ።

ለምእራብ አውስትራሊያ የእኩልነት እድል ደንብ (Equal Opportunity Act, 1984) ግልሰቦችን እድሜአቸውን፤ የጾታ ታሪካቸውን፤ ድኩማንነታቸውን ወይንም ባለባቸው የግል ችግር፤ በትዳራቸው ሁኔታ፤ በፖለቲካ ዝንባሌአቸው፤ በእርግዝና፤ በዘር፤ በሃይማኖት ዝንባሌአቸው፤ በፆታቸው፤ በፆታ ዝንባሌአቸው እና ቀጥሎ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ አድልዎ ማድረግ ሕገ ወጥ ነው።

- ቦታዎችንና መኪና ማግኘት
- መኖሪያ
- ትምህርት
- ቁሳቁሶችና አግልግሎቶች
- መሬት
- የክለብ አባልነት
- ቁሳቁስ ማግኘት
- ሥራ ወይንም ቅጥር

ከላይ የተጥቀሱትን ጉዳዮች አስመልክቶ መድልዎ ተደርጎብኛል ብለው ካሰቡ፤ አመክሮ በመጠየቅ፤ በምእራብ አውስትራሊያ የእኩልነት መብት ኮሚሽነር (Commissioner for Equal Opportunity) ቅሬታዎን ማስገባት ይችላሉ። እባክዎን የእኩልነት መብት ኮሚሽነርን በስልክ ቁጥር 9216 3900 ይጠይቁ ወይንም ለተጨማሪ መረጃ ድህረገጻቸውን www.eoc.wa.gov.au ይመልከቱ።

ስለመድብለባህል ፍላጎት ቢሮ (OMI) ተግባሮችና መርሃግብሮች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፤ እባክዎን፤

የመድብለባህል ፍላጎት ቢሮን ይጠይቁ።

አድራሻቸው፤
Department of Local Government
Gordon Stephenson House
140 William Street
PERTH WA 6000
የስልክ ቁጥር: (08) 6552 1500
ፋክስ: (08) 6552 1555
ኢሜል: harmony@omi.wa.gov.au
ድህረገጽ: www.omi.wa.gov.au